# የትንሾች ትንሽ

ቢበላም ቢጠጣም ፣ ስልጣንም ቢያጅበው
ዘወትር ከቃዡ ፣ ትላንት በተራበው
የፈጣሪን ስራ ፣ በሰው ካሳበበው
አናሳ ነኝ ብሎ ፣ ቅናት ከሸበበው
አይድንም ከህመሙ ፣ ጭራሽ አናስበው ።

አዝሎ ያመጣውን ፣ ከጀርባው ከኋላ
ችግሩን ለመቅረፍ ፣ በዜሮ እያሰላ
ችግር በስራ እንጂ ፣ በዝርፊያ ላይከላ
ጠብ ላይልለት ፣ ከርሱንም ላይሞላ
ካገር ከምድሩ ፣ ሲናከስ ሲጣላ
በስርቆት ካልሆነ ፣ መቼም ሰርቶ አይበላ ።

ወስላታ ወያኔ ፣ አጉል ልማድ ለምዶ
ኢትዮጵያዊነትን ፣ ማንነቱን ክዶ
የጎጠኞች ደዌ ፣ ተጠናውቶት አብዶ
አይቀጡ ተቀጥቶ ፣ ህዝብ ፊት ተዋርዶ
እንዳበደ ውሻ ፣ ካልሆነ ተሳዶ
ሰላምን አያውቃት ፣ መች ይሄዳል ወዶ ።

ተፈጥሮ ባትቸረው ፣ ኑሮው ባይሳካ
ማጀቱ ቢራቆት ፣ በራስ ባይመካ
እንደልብ በልቶ ፣ ጠጥቶ ባይረካ
ችግሩን ተረድቶ ፣ ጋግሮ እያቦካ
አብልቶ ያጠጣን ፣ ሳይሰፍር ሳይለካ
ደግፎ ያቆመውን ፣ ኑሮው እስኪሳካ
ትላንትን እረስቶ ፣ ተብቶ ተመካ
ቀን አነሳኝ ብሎ ፣ አይነኩን ነካካ
ለዘር ለትውልዱ ፣ በቀልን ሊተካ ።

በጥላቻ ቅናት ፣ አይምሯቸው ነቅዞ
ሳይበደል በደል ፣ ቂምበቀል አርግዞ
የትንሾች ትንሽ ፣ ትልቅ ዙፋን ይዞ
በጎጠኞች ደዌ ፣ ሁሉንም መርዞ
የደንቆሮ ሰይፉን ፣ በህዝብ ላይ መዞ
አገር ሲያፈራርስ ፣ ከስሯ ገዝግዞ
ወገኔን ምን ነካው ፣ ይታዘባል ፈዞ
ገፍትሮ እማይደፋው ፣ እጆቹን ጠምዝዞ ።

ታዛቢው

May 12, 2018